+251 (0) 912944937
+251 (0) 930015455
yehaarts@gmail.com
www.yehaarts.com



# ከፈቃዱ ተ/ማርያም(ተዋናይ) ጋር እንጨዋወት

‹በብዙ ቴአትሮች፣ ፊልሞች፣ የሬድዮ ድራማዎችና ትረካዎቹ ያስደመመን፤ አንጋፋው የተዋጣለት ተዋናይ ጋር ማለፊያ ቆይታ ነበረንና እሱን አመስግነን እናንተን ጋብዘናል፡፡›

በታደለ አያሌው || 2015-09-06

## ፩) ትውልድ(ቀንና ቦታ)፣ ቤተሠብ፣ ...

የሐ፡- ቅድመ ቃለ ምልልሳችን ማለፊያ ነበር። ለካ እንዲህ ጨዋታ አዋቂ ነህና?

ፈቃዱ፡- ምን ታደርገዋለህ፣ ካገሩ ነው። ሲልብን ድሮውንም እንዲህ ነን።

የሐ፡- መቼም አንተን ላንባቢዎቻችን እናስተዋውቅ ብንል ማፈራችን ነውና ወደ መሀል ጥያቄዬ ብናልፍስ?

ፈቃዱ፡- እለፍ፤ ማን እንቢ አለህ?

## ፪) ሙያ፣ አስተዋጽዖ፣ ተሰጥዖ

የሐ፡- በዋናነት ተዋናይ ብቻ ነህ ጋሽ ፍቄ። ግን የልብን ስሜት አውጥቶ ለመንገር ተዋናይነት ብቻ በቂ ነው?

ፈቃዱ፡- ሲቻል ነዋ ታዲያ። ጽሑፍ ወይ ሌላ ሙያ ላይ የለሁበትም ያን ያህል። ብችልና እንደሌሎቹም ብጽፍ ደስ ይለኝ ነበር። አሁን አሁን ግን እያሰብኩ ነው። ምክንያቱም በእድሜዬ የካበተ ነገር ስለሚኖረኝ፣ ሌላው ቢቀር የራሴን ታሪክ እንኳን ብጽፈው እላለሁ። ያም ሆኖ ግን እገሌ ስለጻፈ ብየ አልነሳም። እነ እገሌ ስለቻሉ ነው የጻፉት፣ እኔ ደግሞ ይልቁን ትወና ነው የሚሆንልኝ። ይኸ አቢይ እምነቴ ቢሆንም የወደፊቱን አላውቅም።

የሐ፡- ግን የሚያስቀናህ ሙያ የለም? እንዲያው ችየበት ሙዚቀኛ በሆንኩ ኖሮ፣ ችየበት ደራሲ በሆንኩ ኖሮ፣ ሠዐሊ በሆንኩ ኖሮ፣ ... ብለህ የምታሰቀልለት ሙያ የለም?

ፈቃዱ፡- እኔ በተሳካቸው ሰዎች ነው የምቀናው - መንፈሳዊ ቅናት። እንጂ ራሱ እኔ ያለሁበት ሙያ ነው ለኔ ዋናው። ወድጄውም ነው የገባሁበት። ስለዚህ የትኛውንም ጥሩ የሰራ በየትኛውም ሙያ ያለስስት ከማድነቅ ሌላ ይህንን በሆንኩ ብዬ የምመኘው ሙያ የለም። ከሙያዬ ሌላ።

የሐ፡- በእናንተ ጊዜ ኢትዮጵያን ሁሉ ትዞሩ ነበር። ወዲያ አስመራ ሳይቀር በየ ክፍለ ሀገሩ ትዟዟሩ ነበር ቴአትር ልታሳዩ። ያኔ ተችሎ አሁን የተቀዛቀዘበት ምክንያት ምን ይመስልሀል?

www.yehaarts.com

+251 (0) 912944937
+251 (0) 930015455
yehaarts@gmail.com
www.yehaarts.com

ፈ.ቃዱ:- እንግዲህ ምን መሰለህ፣ ትኩረት ቢያጣ ይመስለኛል። እዚህ የተሰሩ ጥሩ ቴአትሮች ሌላውም የሀገራችን ክፍል እንዲደርስ ለማድረግ ተንቀሳቃሽ ቢጠፋ ይሆናል። በፊት ግን እኛ በውሎ አበል 10ብር እየተከፈለን እንዳልከው እንዞር ነበር። ያውም ቴአትር ብቻውን ሳይሆን ከባህላዊና ዘመናዊ ሙዚቃ ጋር ነበር። እና መሄዳችንን ቀድመን ስናውቀው የቴአትራችን ነገርም ቢያንስ ቢያንስ ሀገር አቀፍ ነበር። የጋራ ርዕስ ጉዳይ እናነሳ ነበር። … አሁንም ግን ጨርሶ የተተወ አይመስለኝም። አልፎ አልፎ ተጓዥ ቴአትሮች አሉና።

የሓ:- ትወናን በልምድ ብቻ ነው ወይስ ስርዐትና ጠባዩን ተምረኸዋል?

ፈ.ቃዱ:- ልምድ ብቻም፣ ትምህርት ብቻም አይበቃም። ኹለቱም ሲሆንልህ ነው የሚሞላልህና ትምህርት ባንድም በሌላም ተምሪያለሁ። መጀመሪያ ጋሽ ተስፋዬ አበበ/ፋዘር/ ዘንድ ነበር የገባሁት። ሀገር ፍቅር ‹‹የቴአትር እድገት ክበብ›› ይባል በነበር ጊዜ ማለት ነው። እዚያ ቀዳሚዎች እነ ተሥፋዬ ገሠሠ ሁሉ እየተጋበዙ ያስተምሩን ነበር። ከዚያ ማዘጋጃ ቤት ተቀጠርን። ኋላም ዩኒቨርስቲውና ባህል ሚኒስቴር ተስማምተው ይመስለኛል፣ የተወሠንን ሰዎች ተመርጠን ዩኒቨርስቲ ገባን። እዚያ ብዙ ብዙ አወቅን። ከዚያ ኹለት አመት ተኩል እንደቆየን አሁን በማላውቀው ምክንያት ተቋረጠ። ያም ሆኖ ግን ተጠቅመንበታል። እንዴት እንዴት አይነት ‹ፕሮዳክሽኖች› እንሰራ ነበር።

የሓ:- የምስክር ወረቀት ነገር አለሰጧችሁም ታዲያ?

ፈ.ቃዱ:- እንዳሰብነው አልነበረም ነው እንጂማ የሆነ ወረቀት ሰጠውናል። እኛ ያሰብነው ዲፕሎማ ወይ ከዚያ በላይ ነበር። ግን ዩኒቨርስቲውና ባህል ሚንስቴሩ በመጀመሪያው ልክ አልተባበሩም ነበር። ዞሮ ዞሮ በኋላ እንዳደረኩት የግል ጥረት ስጨምርበት ሙሉ ሆነ።

የሓ:- ብዙ ቴአትሮች፣ ብዙ ፊልሞችና ለቁጥር የሚያታክቱ የሬድዮ ስራዎችን ሰርተሃል። እንዲያው ዞር እያልህ ትታዘባለህ? ‹ይኼን ቴአትር በመስራቴ ማን ምን ተጠቀመ? ባልሰራውስ ኖሮ ማን ምን ይጎድልበት ነበር?› እያልክ ትመዝናለህ ወይስ መስራቴን እንጂ ምን ተዳዬ ባይ ነህ?

ፈ.ቃዱ:- እሠይ! ‹‹ለቁጥር የሚያታክቱ?›› አሁን እንዲህ ይባላል? ለምንድን ነው ደግሞ የሚያታክቱ በል? ይቆጠራሉ እንጂ። ቴአትሮችም የሬድዮ ስራዎችም ምን ቢበዙ እንኳ አንድ ኹለት ተብለው ይቆጠራሉ። /ሳቅ/ … አይ አያለሁ። ያመጣውን ለውጥ አያለሁ። ያኔ በስሜት ወይ በተልካሻ ልዩ ምክንያት የገባሁበትን ብታይ ወዲያው ተመልካቹ አጸፋ ሰጥቶኛል። ‹‹ምን ነካህ›› ሲለኝ እሰማዋለሁ። እኔም ውዬ ሳድር ይህንስ ባልሰራሁት ኖሮ እላለሁ። አሁን ለምሳሌ እኩይ ገጸ ባህሪ ስጫወት ሰው አይቀበለኝም። እኔ ሁሌ ንጉስ ወይ በጎ ሰው ሆኜ ብቻ እንድጫወት ብቻ ነው የሚፈልግ። ይኸ ታዲያ ከስስት የመነጨ ነው። … እኔም ዞር ብዬ ስራዎቼን ሳይ አንዳንዴ ዝም ብሎ ነገሮች አገኛለሁ። ዝም ብዬ አብረን እንስራ ስላሉኝ ሁሉ ለትብብር የሰራኋቸው ስራዎችም አሉ።

የሓ:- ጋሽ ጸጋዬን እንደተዋናይ እንዳንተ የሚያውቀው ሰው ያለ አይመስለኝም። እንዴት ነበር ያንተና የጸጋዬ ገብረመድኅን ጊዜ? መቼም ኹለት ሶስት ቴአትር እሱ ጽፎ አንተ ተውነሃል።

ፈ.ቃዱ:- ኧረ ኹለት ሶስት ብቻም አይደለ። ብዙ ነው። እና በቅርበትም አውቀዋለሁ። አንዳንዴ እንደጓደኛ አንዳንዴ እንደ ሙያ አጋር ሆነን ያሳላፍናቸው ጊዜያት የሚረሱ አይደሉም። በዚያም ላይ ድፍረት ከተባለ የምንዳፈረውም እኛ ነበርን። አሁን ለምሳሌ ቴዎድሮስን ስንሰራ አንድ ቆንሲል ካሜሮን የሚባል ባህሪ አለ። ከእንግሊዝ ኢትዮጵያ ጥያቄና መልስ የሚያመላልስ ሰው ነው። እና ይኸ ሰው ጥያቄ ለንግስት ቪክቶሪያ ልከነው የራሱን ጉዳይ የትም ሲያከናውን ከርሞ ይመጣል። ከዚያ ‹‹የታለ የደብዳቢያችን ምላሽ›› ብዬ -እኔ እንደቴዎድሮስ- በቃሪያ ጥፊ አጣፋዋለሁ። ይኼ ከሆነ በኋላ ኹለት ገጽ ንግግር ያውም ስለ ቁራ የሚያነበንብ ቃለ ተውኔት ጽፏል። ‹‹እህ! ይህንን እንዴት ነው

+251 (0) 912944937
+251 (0) 930015455
yehaarts@gmail.com
www.yehaarts.com

የምለው?›› አልኩት ለጋሽ ጸጋዬ። ‹‹ይህንን በዚህ ስሜት ልለው አልችልም። ጸረ ጡዘት ነው ብዬ እምቢ አልኩ።›› ይህ እንግዲህ ድፍረት ነው በወቅቱ። ከዚያ አዘጋጁ ጋሽ አባተና ገብርዬን ሆኖ የሚጫወተው ገብርዬም ወደኔ አደሉ።

የሓ፡- ምን ይሰማህ ነበር ግን የእሱን ብዙ ድርሰቶች በመጫወትህ? እድለኝነት? ደስታ? …

ፈቃዱ፡- በጣም እንጂ። ትልቅ ደስታ። ለምን ብትል የእሱን ቴአትር ስንጫወት የሆነ ከፍታ/standards/ ይሠጠናል። ከሼክስፔክር እኩል ነው እሱ። የኛ ሼክስፔር ጸጋዬ ገብረ መድኅን ነው። እንዲያውም የእሱን ቴአትር ተጫውተን ሌላ ስንሰራ ከሆነ ንጉሰ ነገስትነት ተሽረን ተራ ገባሪ የሆንን ያህል ይበርደን ነበር። እኔ በተለይ። እንኳን ስለ እሱ ድርሰት ምጥቀት ይቅርና ለኛ ለተዋናዮቹም ለተመልካቾቹም ልህቀት ነበር። እኔ የእሱን ድርሰት ወይ ትርጉም ለመተወን የግድ ወደ እሱ ችሎታ መተካከል ነበረብኝ። የእሱ ድርሰቶች ከተዋናዩም ካዘጋጁም ከታዳሚውም ልዩ ችሎታ ይፈልጉ ነበር። ዋዛ አልነበሩም ክብደታቸው! አሁን ለምሳሌ 70ዎቹ ዐመተ ምህረት ላይ አብዮታዊ ቴአትሮች ነበሩት። እንደ ‹‹ሀሁ በስድስት ወር››፣ ‹‹መልክተ ወዛደር››፣ ‹‹አቡጊዳ ቀይሶ››፣ ‹‹መቅድም››፣ ‹‹ሀሁ ፐፑ›› ያሉት ማለት ናቸው። እኛ እንግዲህ አብዛኛዎችን ተጫዉተናቸዋል። ግን እሱ ይገርምሃል ከባድ ነው። ያሳስትሃል። አንተ በጣም ወገናዊ ሆነህ ‹‹አቤት መንግስትን ወይ እገሌን በአሽሙር ነገረልን!›› ብለን ስንደሰት እሱ ያሰበው ግን ሌላ ይሆናል። በጣም አሻሚ ከመሆኑ የተነሳ ይወሳሰብብን ነበር።

የሓ፡- እሱስ በእናንተ እንዴት ያለ ስሜት ነበረው?

ፈቃዱ፡- እሱማ በእኛ ይረካ ነበር። ከእሱ ደግሞ ይልቁን የምወድለት ነገር ቴአትሮቹ በተመደረኩ ቁጥር ከልምምድ ጀምሮ አብሮን ይገኝ ነበር። ይመጣና ከመድረክ ጀርባ ይዞርና ወደ ሙብራት ክፍል ብቅ ይላል። ከዚያ ይመለስና ለክፎን ወይ ተናግሮን እንደገና ወደ ህዝቡ መሃል ይኼዳል። ቁጭ ብሎ ይመለከታል። እና ራሱ የፈጠረው ስራ እንዲያ ከሌሎቻችን ችሎታዎች ጋር አክለን ስንጫወትለት ደስታው ነበር መቼም። ምናልባትም በእኛ የሚቀና ሁሉ ይመስለኛል። ምነው እኔው ራሴ በተጫወትኩት ኖሮ የሚል ይመስለኛል። አሁን እነ ተስፋዬ ሳህሉ፣ እነ ወጋየሁ ንጋቱ እንዲያ በስሜት እያበዱ እየዘለሉ ሲጫወቱት ሲያይ ገምት የሚሰማውን።

የሓ፡- እሱ ግን ትወና አይሞክርም ነበር?

ፈቃዱ፡- ያዘጋጅ ነበር እንጂ። ባብዛኛው እንዲያውም ሌሎች ቢያዘጋጁት እንኳ እሱም ጣልቃ ይገባ ነበር። ግን በመሰለው ብቻ ስለሆነ የሚያዘጋጅ ከዋና አዘጋጆች ጋር አይመጥንም እምብዛም።

የሓ፡- ኑሮውስ እንዴት ነበር?

ፈቃዱ፡- ኑሮው ጥሩ ነበር። ልጆች አሉት፣ ባለቤቱ አለች። ጥሩ ይኖር ነበር። ምክንያቱም ቴአትሮቹ በየጊዜው ይታዩለት ነበር። አንዱ ለምሳሌ ቴዎድሮስ ብቻ አምስት ስድስት አመት ታይቷል። እና ደህና ነበር ኑሮው። በፊት ደግሞ ባህል ሚኒስቴር ደግሞ ትልቅ ደረጃ ነበረው። ቋሚ ተጠሪ የሚባል ማእረግ። ባንድ ወቅትም የብሔራዊ ቴአትር ስራ አስኪያጅ ነበር።

## ፫) መሰናክሎች፣ ማለፊያ ጥንካሬዎች

የሓ፡- ወደ ሙያው ለመግባት ቀላል ነበር? አሁን በብዛት እንደሚባለው ‹‹ድንገት መንገድ ላይ አግኝተውህ ለዚህ ገጸ ባህሪ ልከኛ ነህ።›› ተብለህ ነው? ወይ ‹‹ካፌ ማኪያቶ ስትጠጣ አይቶ አንድ አዘጋጅ መረጠህ?›› ወይስ እንዴት ነበር?

ፈቃዱ፡- አይ ቀላል አልነበረም። ብዙ ነው የለፋሁ።

www.yehaarts.com

የሓ፡- ጋሽ ጸጋዬ በነገሩ፣ ‹‹ሰው አንድም ሀ ብሎ በፊደል፣ አንድም ዋ ብሎ ባሳር ይማራል›› ይል ነበር። ምን ይቸግርሃል አንተን?

ፈቃዱ፡- አሁን በድንገት ትዝ አይለኝም። ሌላ ጊዜ እነግርሃለሁ።

## ፬) እሱን አጥተን እንዳናጣው ነገር

የሓ፡- ወዳንተ እንመለስና፤ ለምሳሌ መንግስቱ ለማ የእሱንም የአባቱንም ግለ ታሪክ ጽፎ አቅርቧል። አንተስ ሃሳቡ የለህም? ምክንያቱም የአንተን ግለ ታሪክ ብትጽፍ ወይ ብታጽፍ፣ ጎን ለጎን አብረውህ የኖሩና የሰሩ ብዙ ሰዎች ስማና ታሪክ መጠቀሱ አይቀርም። እንዴት ታየዋለህ ይህን?

ፈቃዱ፡- አለ እየተጀመረ ነው። ማለት እንደዚህ የሚያስቡ ሰዎች አሉ። ብትጽፍስ? ብታጽፍስ? የሚሉኝ አሉ። ምክንያቱም አሁን በሚመጣው አመት ጡረታ መውጫዬ ነበር። ግን ትንሽ ሳይጨመርልኝ የቀረ አይመስለኝም። እና ወደዚህ ብዞር ክፉም አይሆን ባይ ነኝ።

የሓ፡- እኛ አገር እንዲያውም ደግ አይበረክትልን። አንተስ እንዲያው እድሜህም ቀላል አይደል። እና በድንገት አጥተንህ ወይኔ ከምንል ኑና ከኔ ምን ውሰዱ ትለናለህ?

ፈቃዱ፡- ሰው መቼም ያለውን ነው የሚሰጠው። እስካሁን ስኖር የሰማሁትን ያየሁትንና የታዘብኩትን ለወጣቶቹ ባካፍል ደስ ይለኛል። አመጣጤንና እድገቴን ልክ እናንተ በያዛችሁት መንገድ ለማስተናገድ አስባለሁ። በግል ደግሞ ወጣቶች ሲጠይቁኝ እምቢ አልልም። እታዘዛለሁ። ምክንያቱም ወጣትነት ከባድ ነው። አላማ ቢስ እንዳይሆኑ መስመር ለማስያዝ እሞክራለሁ።

## ፭) መርሆች፣ የህይወት ፍልስፍናው

የሓ፡- አንዴ ባህርዳር ባለው ሙሉዓለም ባህል ማዕከል መጥተህ ፊት ለፊት ስትናገር ሰማሁህ። ‹‹ግቢውን አረንጓዴ አድርጉት እንጂ፣ … ስብሰባ አታብዙበት፣ … ወጣቶች ራሳችሁን ጠብቁ፣ …›› እንዲህ በደረቁ ፊት ለፊት ስትመክር ሰምቼሃለሁ። እንዴት ነው አስተያየትህ?

ፈቃዱ፡- ኧረ ሲጀመር ሙሉዐለም አልመጣሁም ተው?

የሓ፡- መጥተህማ ‹‹የቴዎድሮስን ስንብት›› ሁሉ ትንሽ ብለንልሃል። መምጣቱን መጥተህ ነበር።

ፈቃዱ፡- ማን ነው ያለው?

የሓ፡- ይኸው እኔ። ነበርኩ እኮ በጉባዔው።

ፈቃዱ፡- ዉሸት። አትከራከረኝ በከንቱ። ይልቅ ባህር ዳር ሌላ አዳራሽ ላይ ተገኝቼ አውቃለሁ። ያኔ እነማዲንጎ ሁሉ ነበሩ። አርበኞች ነበሩ። እኔ ደግሞ ቴዎድሮስን ትንሽ አነብንቤ አርበኞች ሁሉ እንባቸው መጥቶ እንደነበር ትዝ ይለኛል። ታዳሚው ሁሉ። እና ሙሉዓለም ጥሩ ባል ማዕከል እንደሆነ እሰማለሁ እንጂ አልመጣሁም።

የሓ፡- ግዴለም እሸነፋለሁ። ግን አስተያየት ላይ ወዴት ነህ?

www.yehaarts.com

ፈቃዱ፡- አስተያየት ላይ ፊት ለፊት የምሆነው ለአድናቆት ሲሆን ብቻ ነው። አድናቆት ላይ ንፍገት የለኝም። በደስታ በሰው ፊት ቆሜ ነው የማደንቅና የማመሰግነው። የማላውቀው ሰው ቢሆን እንኳ። ነቀፌታዬን ግን ጥንቃቄ አበጅለታለሁ። ስሜት ላለመጉዳት እቸገራለሁ። ‹‹እንዲህ›› ብለውስ ‹‹እንዲያ›› ቢከፋውስ እላለሁ። ዞሮ ዞሮ መናገሬ ባይቀርም።

የሓ፡- ፖለቲካ ላይስ እንዴት ነህ? እድሜህ እኮ ይፈቅዳል።

ፈቃዱ፡- እኔ አላውቅበትም። ወደፊትም ቢሆን ምንም ቃል የምገባው ነገር የለኝም። እድሜህም ይፈቅዳል ያልከው ተደራጅተህ ፓርቲ መስርት ለማለት ከሆነ አልችልበትም።

የሓ፡- አይ አይ። እድሜህና ደረጃህ የሚፈቅደውማ ለሚዛናዊነቱ። እንዲህ ጽንፍና ጽንፍ የሆኑ የፖለቲካ ክርክሮች ሲነሱና እድሉን ስታገኝ ሽማግሌ ለመሆን ማለቴ ነው። በዉይይቶች መሃል፣ በጨዋታዎች መሀል፣ ወዘተ። ‹‹ሰው መቼም በኢኮኖሚ እስካለ ድረስ ከፖለቲካ አይወጣም›› ይባላልና።

ፈቃዱ፡- ኧረ ምኑን አውቄው ጃል።

የሓ፡- አንዳንድ የዕምነት እንቅስቃሴዎች ላይ አይሃለሁ። በተለይ ‹‹የቅዱስ ጊዮርጊስን›› ታሪክ ከእነ አበበ ፈለቀ፣ መሠረት መብራቴ እና ሌሎች ሆናችሁ ጥሩ ተርካችሁታል - የትርጉም ፊልሙን። እንዴት ነህ በእምንት በኩል?

ፈቃዱ፡- እምነትማ ያው የግል አይደል። መቼስ ላንዲት ነፍሳችን … እሱ ደስ ይለኛል። ሰው ፈሪሃ እግዚአብሔር ሲኖረው ልክ ይገባል። ‹‹የጥበብ መጀመሪያው እግዚአብሔርን መፍራት ነውና››።

የሓ፡- ለዛሬ ይህን ይመስላል። በምርቃት እንለያይ?

ፈቃዱ፡- ምን ያህል የምትፈልገውን ነገር እንደሰጠሁህ አላውቅም።

የሓ፡- እኔም ምን ያህል የምፈልገውን እንደጠየኩህ እንጃ። ብቻ እያደር ‹‹ይህን በጠየኩት ኖሮ›› የሚል ጥያቄ እንደሚኖረኝ እገምታለሁ።

ፈቃዱ፡- ታዲያ ያኔ አለሁ። በእናንተው ቋንቋ፤ ‹‹አንፋታም›› …

የሓ፡- እውነት ያድርገው። አይለያየን። ያገናኘን። ያክብርልን።

ፈቃዱ፡- አሜን!

## ፺) ምንጮቻችን

ቀጥተኛ ቃለ ምልልስ፣ የሓ ቤተ ጥበብ

www.yehaarts.com